ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2017/12

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

የአሜሪካ መንግሥት በመቀሌ አዲስ ክልላዊ የኅብረተሰብ ጤና ላቦራቶሪ አስመረቀ

አዲስ የተገነባው ላቦራቶሪ በክልሉ ሆስፒታሎች እና የጤና ማዕከላት ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች የጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት ይሰጣል

መቀሌ፤ ትግራይ፤ ግንቦት 17፤2009፤- በአሜሪካ ፕሬዚዳንት የአስቸኳይ ዕቅድ ለኤድስ ድጋፍ (PEPFAR) የገንዘብ ድጋፍ በአሜሪካ መንግሥት የበሽታዎች ቁጥጥርና መከላከል ማዕከል (ሲዲሲ) የተገነባውና በኢትዮጵያ አራተኛው ዘመናዊ የክልል ሪፈራል የኅብረተሰብ ጤና ላቦራቶሪ ማዕከል ተመርቆ ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዛሬ በይፋ ተላለፈ፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ የበላይ ጉዳይ ፈጻሚ ፒተር ቨሩማን ከአቶ ዳኒኤል አሰፋ፤ የመቀሌ ከተማ ከንቲባ እና ሌሎች የክልሉ መንግሥት እና የአሜሪካ ኤምባሲ ተወካዮች ጋር በመሆን አዲሱን ማዕከል መርቀዋል፡፡

3.5 ሚሊዮን ዶላር ወይም 80 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገለት ክልላዊ የኅብረተሰብ ጤና ማዕከል፤ በትግራይ ክልል እና በሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙ አምስት ሚሊዮን ለሚጠጉ ሰዎች አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ማዕከሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ፤ ቲቢ እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር እና ህክምና ከማጠናከር በዘለለ፤ በኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ድንገተኛ ምላሽ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በክልሉ ሆስፒታሎች እና የጤና ማዕከላት የሚገኙ ላቦራቶሪዎችም በማዕከሉ የውጭ የጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በተጨማሪም፤ ማዕከሉ ለላቦራቶሪ ባለሙያዎች በኤች አይ ቪ /ኤድስ ህክምና፤ በቲቢ፤ ወባ፤ የኤች አይ ቪ ባይረስ ክምችት እና ጥራት ክትትል ሥርዓት ላይ ሥልጠና የሚሰጥበትን መድረክ ይፈጥራል፤ ለክልሉ የኅብረተሰብ ጤና ምርምር ተቋም በመሆንም ያገለግላል፡፡

በ1,500 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተገነባው ባለሁለት ወለል ዘመናዊ የላቦራቶሪ ማዕከል፤ ዓለም አቀፍ የግንባታ መስፈርቶችን ያሟላ፤ በዘመናዊ የላቦራቶሪ ቁሶች የተደራጀ እንዲሁም በማራኪ ንጣፎች የተዋበ እና ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የህንጻ ግንባታ ሂደቶችን ያለፈ ነው፡፡ የአየር ማቀዝቀዣ፤ ጀነሬተር፤ ማቀዝቀዣ እና ቲቢ ሊኪዊድ ካልቸር ላብ ተሟልቶለታል፡፡

የማዕከሉ ግንባታ የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ የጤና መሠረተ ልማትን ለማጠናከርና ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመዋጋት የወጠነው የረዥም ጊዜ ውጥን አካል ነው፡፡ ላለፉት 15 ዓመታት የአሜሪካ መንግሥት በበሽታዎች ቁጥጥርና መከላከል ማዕከል (ሲዲሲ) በኩል ለኢትዮጵያ መንግሥት የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት በሀገር አቀፍ፤ በክልሎች እና በተቋም ደረጃ የተሻለ የላቦራቶሪ አገልግሎት እንዲኖር ድጋፍ አድርጓል፡፡ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመግታት፤ የአባለዘር በሽታዎችን፤ ቲቢን፤ የተከሰቱ እና ሊከሰቱ የሚችሉ ወረርሽኞችን የመከላከል ሚና ለነበራቸው መርሐ-ግብሮችና የቁጥጥር ሥርዓቶች ድጋፍ አድርጓል፡፡

###